# <u>የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በታህሳስ ወር 2009 ዓ.ም. ያወጣው "የራስ አገዝ የመኖሪያ ቤቶች ህብረት ስራ ማህበር" ማስፈፀሚያ ማንዋል ይዘት ዋና ዋና ነጥቦች</u>

- በክልሉ መመሪያ ቁጥር 3/2009 መሰረት በውጭ ሃገራት ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተዘጋጀው አዲስ ማንዋል በክልሉ ስር በሚገኙ 12 ታላላቅ ከተሞች ተግባራዊ የሚሆን እንደሆነ፣
- ከእነዚህ ከተሞች መካከልም ዋና ዋናዎቹ መቐለ፣ አላማጣ፣ ኮረም፣ ማይጨው፣ ዓቢይዓዲ፣ ውቅሮ፣ ዓዲግራት፣ ዓድዋ፣ አክሱም፣ ሽረ-እንዳስላሰ እንዲሁም ሽራሮና ሑመራ እንደሆኑ፣
- በፕሮግራሙ ተጠቃሚ መሆን የሚፈልጉ ማህበራት የሚደራጁት በሚሲዮኖቻችን አማካይነት ሆኖ የተደራጁ ማህበራትን መረጃ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የዳያስፖራ ተሳትፎ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጄኔራል በኩል ለክልሉ ማሳወቅ እንደሚገባ፣
- የፕሮግራሙ ተጠቃሚ ለመሆን በመጀመሪያ በዝግ ሂሳብ በባንክ በውጭ ምንዛሪ ለቤቱ መስሪያ የሚሆን ግምት ገንዘብ ማስቀመጥ እንደሚያስፈልግ፣
- የቤቱ ግምት ዋጋ 240,000 (ሁለት መቶ አርባ ሺህ) ብር ሆኖ በተመጣጣኝ የውጭ ምንዛሪ የሚቀመጥ እንደሆነና ግምት ዋጋው የቤት ውስጥ ፊኒሺንግ ስራዎች የማይጨምር እንደሆነ፣
- የማህበር አባላት 20 መሆን እንዳለበት (ከሽራሮ ሑመራ ውጭ)፣
- የማህበር አባላት 16 መሆን እንዳለበት (ለሽራሮ ሑመራ)፣
- 20 አባላት ላሉት ማህበር የቤቱ ስፋት 1400 ካሬ ሜትር እንደሆነ፣
- 16 አባላት ላሉት ማህበር የቤቱ ስፋት 1600 ካሬ ሜትር እንደሆነ፣
- ህንፃው ባለ አንድ ፎቅ (Modern Town House) እንደሆነ፣
- በባንክ በዝግ ሂሳብ የሚቀመጠው ገንዘብ ስለሚለቀቅበት፣ የግል ካርታ ማግኘት ስለሚቻልበት ሁኔታ፣ በፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች መሟላት ስላለባቸው ቅድመ-ሁኔታዎች እንዲሁም በማህበሩ አባላት የሚሞሉ ቅፆችና ሌሎች ጉዳዮች በማስፈፀሚያ ማንዋሉ የትግርኛ ቅጂ በስፋት የተብራሩ መሆኑን እንገልፃለን፡፡